# ተዋውለው (ግጥም)

ከቴዎድሮስ ታደሰ መንግስቱ

ሰው መሆኔን እረስተው

ከሰው ገንዘብን አስቀድመው

ገንዘብና ሰው በአንድላይ ወድቀው

ሰውን ጥሎ ገንዘብን አነሳው

ተብሎ  የተዘፈነለት ወያኔ ሞጭላፋው

እያስመሰለ በዛ አለባልታው

ኖርዌ`ይ ማስመሰሉን ግጥም አርጋ  አውቃው

ጭንቀት መከራየን ረስታው

ሰብ አዊነቴን  እረግጣው

አላምጣ አኝካው

ለብዙ ዘመን አሽታው

ልቢን ሰጥቻት አብሪኣት ኑሪው

ለአውሬው ለነብሰገዳይው

በገንዘብ ኖርወይ ልትለውጠኝ ተስማምታው

ዲክታተሩም ይችልበታል ለማስመሰሉው

ያ  በውሽት ተረግዞ  በውሽት የተወለደው

የእንግዲህ ልጅ የሆነው

በዘር ያታጀበው

ፋሽሽስትነቱን ለኣለም ብንነግረው

ጀሮ ዳባ ብለው

እኔ እያለው ባለቤቱ ዜጋው

ሚስጥሩን የማውቀው

የወያኔን ተንኮል አለባልታው

ሊያስረዱኝ ሊነግሩኝ ብለው መለስ ጭዋ ነው

ሆኖብኝ ልጅ ለእናቷ ምጥ ኣስተማረቻት እንደሚባለው

ሰው በሰፈረው ቁና መሰፈሩን እረስተው

በዘመናዊነት በጊዜ ተማምነው

በጊዜ ተኩራርተው

ዋ ጊዜ እንድሆን ሳሙና ነው

ከፍ ዝቅ እያደረገ ሲያመቻቸው

ሲሰፍረው ሲለካው ሲሰፍረው ሲለካው

እርሱ ያቅበታል ጊዜ ብልጥነው

አሽከርክሮ አንደርድሮ ሲጥለው

ሆኖ እንዳይቀር እንዳተባለው

ጉምን የዘገነና ጊዜን ያመነው

መች እንዲሁ ወፍዘራሽ ነን

ሀገርማ አዎ ሀገር አለን

ህዝብም የሚወደን

ቤተሰብም የሚያከብረን

የተሰራን በእግዚኣብሄር ቃልኪዳን

ድህነትም እርሀብም አያስፈራን

ዲሞክራሲ ሰላም ካለን

በስራ በጥረት እናድጋለን

አሁን እኛን የቸገረን

ሰላም ዲሞክራሲ ማጣት ተደራጅተውብን

የዲክታተሩ አገዛዝ አንገፍግፎን በቃ ለስደት ተደናቀፍን

ዛሬም ነገም ብንገልፅ እውነትን

ብናለቅስ ብንጮሕ ብንነግር ዲክታተርነቱን

ከምንም ሳይቆጥሩ ተስማምተው ሊጭኑን

እንደ እቃ  ግምት አውጥተው

ሰው መሆኔን እረስተው

ሊጭኑኝ ተስማምተው

ለዲክታተሩ ለአውሬው

በአለም እንደሚታወቀው

ስለኖርወይ ሰብ ኣዊ መብት የተወራው

የት ገባ አሁን ያ ሰብ አዊ መብትው

የሰውልጅ እረክሶ በገንዘብ ሲለወጠው

አብረን በኖርወይ በሆዶኣ ኑረነው

ባህሏን ኣውቀን ከህዝቡ ተቀላቅለነው

እኮ ኖርወይ የት ጠፉ ያ ባህልሽ ሰብ ኣዊ መብቴው

ኖርወይ በአደባባይ የሞትፍርድ ፈርዳብን

ገፍታ ጥላ ወደእሳት ልትማግደን

ኡ  እያልን

ብንጮሕ ብናለቅስ ሞትን ፈርተን

በተግባርም ብንገልፅ በርሀብ አድማን

እኮ ማን ያዳምጥን

ብናለቅስ የኖርወይ ህዝብ ብለን

ኡ ኡ ኡ ኡ እያልን

ድረሱልን ሳንሞት ሞትን

አለ ሲኦል አፉን ከፍቶ የሚጥብቀን

የሚዝናና በማሰር ሰውን

የሚደሰት በመግደል ሰውን

እንደእውነት አርጎ የሚያቀርብ ውሸትን

ለክፉ ሃሳብ የተፈጥረ አእምሮው የሚያፈልቅ ተንኮልን

ይህንን እያዩ እነምእራብያዊያን

ጋዜጠኞች የታሉ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን

እነዛን ለዲሞክራሲ ለሰላም የታገሉትን

እስር ቤት ማግዶ ገሎ የቀሩትን

እውነት አጥታው ነው ኖርወይ ይህንን

አጥብቄ እለምናለሁ ኖርወይ አትጨክኝብን

ሰላም ሰፍኖ ሃገራችን

እስከምንመለስ ሆኖ እርአያችን

ኖርዌይ እባክሽን አሳልፈሽም አትስጭን

ጊዜ እስከሚያልፍ መጥጊያ ስጭን

በውሸት ሰግዶ

በማስመሰል አሰግዶ

ወገኖቹን አርዶ

ኮሮጆውን በገንዘብ ሞልቶ

አላማው የታወቀ ጎልቶ

በዲክታተርነቱ በፋሽሽስነት ከርፍቶ

ኖርወይ በአለም  የታወቀች በሰባዊነት

እኮ ምን አመጣው ከዲክታተር ጋር ህብረት

ኖርወይ ይግባሽ የኔ ስደት

ተራው የኔ ሆኖ በቃ ድንገት

ሰላም ዲሞክራሲ ማጣት

ብጥይቅ ጥለላ ህይወቴን ላቆያት

ለኖርወይ ወንጀል ሆኖ ታይቶብኝ ስደት

ዛሬም ነገም ባለቅስባት

ጭክና ከዲ ክታተር ጋር ኮብልላ

ያን መልካም ባህሏን ጥላ

ምስኪኑን እኔን ስደተኛውን አባብላ

ልትለውጠኝ በገንዘብ ተዋውላ

ሰብ አዊ መብቴን ጭፍልቃ ገላ

በሰውደም  በገንዘብ ቆቱ ለማይሞላው

ለዛ ነብሰ ገዳይ ኖርወይ ልታቀብለው

ዋ  ኖርወይ እለምንሽ አለው

ማሰቡ አይከፋም እንዳንጠላላው

ትውልድ እንዳይጠይቅሽ የወደዋላው

ግራገብቶኝ ስጉላላ እኔ ስደተኛው

ሊለውጡኝ በገንዘብ ተዋውለው

አዋ  ተዋውለው

ተዋውለው ተዋውለው

ተዋውለው ተዋውለው

ተዋ ው ….ለ….ው

ቴዎድሮስ ታደሰ መንግስቱ

08 02 2012

ኖርዌይ ኦስሎ

ማስታወሻነቱ  ኖርዌይ ኢትዮጵያዊያንን ለዲክታተሩ መለስ ለማቀበል የምታደርገውን ጫና በቆራጥነት ተቃውሞን በመግለፅ እንዲሁም ግፍ የደረሰባቹህ ወገኖቸ በሙሉ ይሁን